★ዴሞክራሲያ★

ዴሞክራሲያ ቅጽ 33 ቁጥር 6 መጋቢት 2000 ዓም

# ሴት ልጅ ከታገለች የድል ቀን ቀረበች

*በማንኛውም ሀገርና ኅብረተስብ ውስጥ በታሪክ፥ ሴት የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል እንደነበረች አሁንም እንደሆነችና ወደፊትም ይህ ሁኔታዋና ደረጃዋ ህያው ሆኖ እንደሚቀጥል ለክርክር የሚቀርብ አይደለም። በአካልነቷም በዓለም ለተከናወኑት ሥልጣኔዎች፥ የዕድገትና የልማት ዕርምጃዎች ሁሉ የሚጠበቅባትን ግዳጅ ስትወጣ ኖራለች። በታሪክ ሂደት በኅብረተሰቡ ውስጥ ስታደረገው የቆየቸው ተሳትፎ እንደ የባህሉና እንደ የሥርዓተ ማኅበሩ ሁኔታ ከሀገር ሀገር ሊላያይ ቢችልም፥ በመሠረቱ፥ ሴት ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከተችው ባህላዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ኅብረተ ሱታፌ ዓለም አሁን ለደረሰችበት ደረጃ ህያው ምስክር ነው። የማንኛውም ኅብረተሰብ መሠረቱ ቤተሰብ እንደ መሆኑ፥ ሴት ለቤተሰብ አልፋና ኦሜጋ ነች። በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ የሚከበረውን የሴቶች ቀን በዓል ስንዘክር፥ ሴት ከቤተሰብ አንስቶ እስከ ሀገር ደረጃ ድረስ የምታበረክተውን ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠውን አገልግሎትና የምትጫወተውን ሚና አንፀባራቂ ኮከብ የሚያደርጋት መሆኑን በማመን ነው። ሴት የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ነች ሲባል አባባሉ፥ ለአሃዝ ማሚያና ለስታትስቲክ ሰንጠረዥ መመዝገቢያ ሳይሆን፥ በዕርግጥም ሴት ለኅብረተሰሰቡ አዕምሮዋን፥ ነፍስና ስጋዋን፥ ጉልበቷንና ብልሃቷን፥ ፍቅሯንና ርኅራሄዋን፥ ሀዘኔታዋንና ይቅርታዋን በጠቅላላው አነጋገር ሁለመናዋንና ህይወቷን ለቤተሰቧና ለኅብረተሰቡ ያበረከተች ሰብዓዊ ፍጡር ነች ማለት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።*

*ሴት በሰብዓዊ ፍጡረነቷ ለኅብረተስቡ ሁሉ በግማሽ አካልነቷ ተዘርዝሮ የማያልቅ ጠቃሚነቷ የታወቀ መሆኑ የሚያከራክር ባይሆንም፥ የሚገባትን ሁሉ ዕውቅናም ሆነ እንክብካቤ አልተነፈጋትም ለማለት የሚቻል አይደለም። የበደሏና የችግሯ መጠን እንደየ ሀገሩና እንደ የባህሉ ይለያይ ይሆን እንደሁ እንጅ፥ በሴትነቷ ብቻ በዘመናት ልዩ ልዩ ጥቃት እንደተፈፀመባት የሚክድ የለም። ከታሪክ፥ ከባህል፥ ከሃይማኖትና ከኋላ ቀርነት የመነጨ ከንቱ አስተሳሰቦች ተደራርበው ባመጡባት ተፅዕኖም፥ የእነርሱ ሰለባ ከመሆን አልዳነችም። ከፖለቲካ ከኢኮኖሚውና ከማኅበራዊ በኩል የሚገጥማት ጥቃትና እንግልትም ለሰቆቃዋ ተጨማሪ ሀዘኔታን አክለውባታል። ይህን ክስተት በመላው ዓለም የሚገኙ ሴቶች ይጋሩታል። በመሆኑም፥ ከጭቆናቸው ለመላቀቅና በኅብረተስቡ ዘንድ የሚገባቸውን መብትና ነፃነት እኩልነትና የዜግነታቸውን ማንነት ለማረጋገጥ፥ በዘመናት ሲታገሉ ለመኖራቸው በብዙ ማስረጃዎች የተደገፉ መጻሕፍት ተደርሰዋል። ሴቶች በአከናወኑት መራራ የመብት ጥያቄ ትግል ምክንያት በተጎናጸፉት ነፃነትና በእኩልነት ያገኙትን ዕድል በመጠቀም፥ ከወንዶቹ ጋር መሳ ለመሳ በመሰለፍ፥ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፥ በሥነጥበብና በምርምር፥ በህንፃና ቅርፃ ቅርፅ ተግባር፥ በእርሻና ንግድ፥ በሀገር ግንባታና መከላከያ፥ በነፃነት ትግል በመሳሰሉት የበኩላቸውን ድርሻ በመወጣት ችሎታቸውንና አገልግሎታቸውን አስመስክረዋል። ይህ ግን ሴቶች በቤተሰብ ኃላፊነታቸውና በእናትነታቸው ከሚያበረክቱት አገልግሎትና በኃላፊነት በተጨማሪ መሆኑን ለደቂቃ እንኳን ሊሳት የማይገባው ለመሆኑ በማስገንዘብ ነው። የግል ነፃነትንና መብትን ያህል ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠውን ክቡር ጉዳይ በቀላሉ የማይገኝ መሆኑን በመገንዘብ በዓለም የሚኖሩ ሴቶች፥ ነፃነታቸውንና*

ክብራቸውን ለማስረገጥ ሲሉ ከፍተኛ መሥዋዕት መክፈላቸው ተጨማሪ ክብርንና ሞገስ እንዲሁም በራስ ልዕልና የመተማመን ልበሙሉነት አጎናጽፏቸዋል፡፡ ይህ ማለት ግን በመላው ዓለም የሚኖሩት ሴቶች በሙሉ ይህን ዕድል አግኝተዋል ማለት አይደለም፡፡

የሴቶች ጥያቄ ከሰብዓዊ መብትና በጠቅላላውም ከዴሞክራሲና ከኢኮኖሚ ጥያቄዎች ጋር የተየያዘ በመሆኑ፥ በመሠረቱ የሴቶቹ ጥያቄ የፖለቲካ ጥያቄን ሁሉ ያካትታል፡፡ የፖሊቲካ የኢኮኖሚና የማኅበረሰባዊ ነክ የሆኑ ጥያቄዎች በአግባቡ መልስ ሊያገኙ የሚችሉት ደግሞ፥ በአንድ ሀገር የሚኖሩ ዜጎች፥ በፆታና በሃይማኖት ወይም በዘርና በቋንቋ መስፈርት ሳይመደቡ ሁሉም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤቶችና ለዚህ ሥርዓትም ተገዥዎች ሲሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት የሴቶች ጥያቄ በመሠረታዊና ዘለቄታ መልኩ መልስ የሚያገኘው፥ የዚያ ሀገር ዜጋ ሁሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሲከበሩለትና ሲረጋገጡለት ማለት ነው፡፡ ይህ ሐቅ ዓለም-አቀፍ ይዘት ስላለው፥ በአንድ ሀገር ድንበርና ክልል የሚወሰን ሊሆን አይችልም፡፡ ሁሉም ዜጋ የተሟላ ነፃነቱን ካላገኘ ደግሞ ሴቶች በፆታቸው ብቻ የሚፈፀምባቸው ጭቆናም ይሁን ግፍ ብቻውን መፍትኄ አያገኝም፡፡ ሴቶች የኅብረተ ሰቡ ግማሽ አካል መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ ከወንዶች ጋር ከሚካፈሉት የዴሞክራሲ ማጣት ጭቆና በላይና ባሻገር፥ በተለየ መልኩ በፆታቸው ምክንያት ግፍ ስለሚያጋጥማቸው ሴቶች ድርብ ጭቁኖች ናቸው የሚባል መለያ አላቸው፡፡ ይህ መለያ ደግሞ ለሰበዓዊ መብት መጣስ ተቆርቋሪ ከሆነው ክፍል ትብብርንና ሀዘኔታን አስገኝቶላቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ አንድ ሌላ ትልቅ ጥያቄን ወደሚያስከትል ምዕራፍ ለማተኮር ምክንያት ይሆናል፡፡ይኸውም፥ ለማነኛውም ሀገር የፖለቲካ ፥ የኢኮኖሚ የማኅበረሰባዊና የሰብዓዊ መብቶች ጥያቄዎችና ችግሮች መልስ ሊያስገኙ ወደሚያስችሉ የመፍትኄ ፍለጋ ጎዳና ማምራት ነው፡፡ ወደዚህ ጎዳና ማምረት የሚቻለው፥ ዘላቂ ሠላምንና መረጋጋትን ሊያመጣ ወደሚያስችለው መሠረታዊው የፖለቲካ መፍትሔ ላይ መረባረብ ሲቻል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሁሉም ዜጋ ተደጋግሞ እየጮኸበት የሚገኘው የዴሞክራሲ ጥያቄና የሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን የዓለም ሀገሮች ኅብረተሰብ አባል እንደመሆኗ ፥ ጥያቄው እርሷንም በቀጥታ ይመለከታል፡፡ የሀገራችን ሴቶች በፆታቸው ብቻ የሚፈፀምባቸውን የቆየ ችግርም ከዚህ ተለይቶ ማየት አይቻልም፡፡

ታዲያ የሀገራችንን ሴቶች ሁለንተናዊ ችግር ስንመለከት አያሌ ጉዳዮችን ከተለያዩ አንፃሮች እየተመለከትን መወያየት እንችላለን፡፡፡ ከላይ ስለ ዓለም ሴቶች በኅብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚናም ሆነ ስለ ሚደርስባቸው በደል ያነሳናቸው መሠረታዊ ነገሮች ሁሉ፥ እንደዚሁም የሀገራችን ሴቶችም ችግሮች መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፥ የኢትዮጵያ ሴቶች መራራ ኑሮ የተላበሰውን ግፍና ሰቆቃ በተለየ መልኩ ማንሳት ግን ሰብዓዊነታችን ብቻ ሳይሆን፥ የዜግነት ኃላፊነታችንም ያስገድደናል የሚል የጎሊና ጥያቄም አለብን፡፡ በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩትን እናቶቻችንንና እህቶቻችንን መራራ ህይወትና የተሸከሙትንም ከባድ ቀንበር ስንመለከት፥ በሃያ አንደኛው ምዕት ዓመት በዓለም ከሚኖሩ የዓለም ሴቶች እጅግ በከፋ የጨለማ ኑሮ ይናራሉ ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ ይህንንም ገላችንን ሰድደን ለማለት የበቃነው፥ ፓርቲያችን ኢሕአፓ ትግሉን ሲጀመር ካነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች አንዱ፥ የሀገራችንን ሴቶች ስር የሰደዱ ሁለንተናዊ ችግሮችን ለመፍታትም ጭምር በመሆኑ ነበር፡፡ የሀገራችን ሴቶች ችግር፥ ከሀገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች ጋር በብዙ ሀብል የተየያዙ በመሆናቸው ችግሮቹ ሁሉ እስካሁን ድረስ ሳይፈቱ በመቅረታቸው ብቻ ሳይሆን፥ እንዲያውም በበዛ መልክ እየተባባሱ ያሉ መሆናቸውን ስነገነዘብ፥ የቱን ያህል የህሊና ሰቆቃና የልብ ቁስል እንደሚሰማን በማወቃችን ነው፡፡ የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴቶች የጨለማ ህይወት፥ በዓይናችን የተመለከትነውና ህይወቱን በቦታው በመገኘት የተካፈልነው በመሆኑ፥ ብሶታቸው ብሶታችን፥ ሰቆቃቸው ሰቆቃችን እንደሆነ ይሰማናል፡፡ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነንና የሚያበሳጨን ደግሞ፥ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የኖረው የሀገራችን ሴቶች መራራ ህይወት አሁንም በከፋ መልኩ መቀጠሉ ነው፡፡ በዓላማችን ፀንተን እንድንታገል ካስቻሉን መሠረታዊና ዓበይት ምክንያቶችም አንዱ ይህ በተፈራረቁት ሥርዓቶች መፍትኄ ያልተገኘለት የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴቶች አሳዛኝ

ህይወት ነው::

የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴት ኑሮ ከፀሀይ መፍንጠቅ እስከ ጮራዋ መጥለቅ ድረስ ያለ ዕረፍትና ፋታ፥ ጎንብስ ቀና እያለች ያለመታከት መልፋት ነው:: ጧት ወፍ ሳይጮኽ ተነስታ ለባሏና ለልጆቿ የሚሆን ምግብ በማሰናዳት እነርሱን ወደ እርሻና ወደ ከብቶች ማሰማራት በኋላ፥ የቀረውን የቀኑን ጊዜዋን የምታሳለፈው፥ ወፍጮ በመፍጨት ውሃ ለመቅዳት ብዙ ምዕራፍ ርቀት ያለውን ጉዞ በመሄድ፥ በጀርባዋ እንስራ በመሸከም ውሃ ይዛ ወደ ቤቷ በመሄድ፥ የማገዶ እንጨት በመልቀም፥ ወደ መምሸቱ ገደማ ያለውን ወቅት የምታሳልፈው ደግሞ ለቤተሰቧ ዕራት በማብሰልና በመመገብ ይሆናል:: ከዕራት በኋላ ቤተሰቡ ሁሉ ሲተኛ፥ አሁንም ዕረፍት የላትም:: ቤተሰቡን ማልበስ ኃላፊነቱ የእርሷ በመሆኑ፥ እስከ መንፈቀ-ሌሊት ድረስ ጥጥ ስትፈትል ስለምትቆይ፥ ለዕንቅልፍ የሚተርፋት ጊዜ እጅግ በጣም ጥቂት ይሆንባታል:: በዚህ ላይ ሕፃናቱን የማሳደግና የመንከባከብ ኃላፊነት ለእርሷ ብቻ የተሰጠ ተግባር ነው:: ህፃኑን ልጇን ከመደቡ ላይ አስተኝታ ስትፈጭ ልጁ ትኩሳት ይዞት ካለቀሰባት የእናት ርኅሩኅ አንጀቷ ስለማያስችላት ልጇን ያባበልች እየመሰላት በጀርባዋ አዝላ መፍጨቷን ትቀጥላለች:: ከአዘለችውም በኋላ ማልቀሱን የሚቀጥል ከሆነ፥ በእናት ርኅራኄ እያቆላመጠች ትዘምርለታለች:: እግረ መንገዷንም የራሷን ሰቆቃ አብራ ትገልፃለች:: እንዲህ እያለች:-

> " ስፈጭም አዝየ፥ ሳቦካም አዝይ፥ ስጋግር አዝየ፥
> እራበህ መሰለኝ ና ውረድ ማሙየ፥
> አንተስ አይመምህ እስቲ አታልቅስብኝ፥
> አንተንስ ከሚያምህ እኔን ክምብል ያርገኝ:: "

በእናትነቷ ህፃናቱን የመንከባከብና የማሳደግ አላፊነቷን ከመወጣት አልፋ ተርፋ፥ የሚስትነቷም፥ ግዴታዋን ለመወጣት የባሏን ፍላጎት የማርካት የተፈጥሮ ግዴታዋ እንደሆነ ይወሰድባታል:: እግሯን ከአቃቅማ፥ የሚከላከልላት ጫማ፥ ሰውነቷን ከብርድና ቁር የሚጋርዳት በቂ ልብስ ስለማይኖራት፥ ገና በወጣትነቷ ውበቷ ጠውልጎ፥ ፊቷ ገርጥቶ ፥ የችግር ኑሮዋን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ትገፋዋለች:: ላጊጥ ልሽቀርቀር የሚል ምኞት አታስተናግድም:: ዝም ብላ መድከም ፥ መልፋት! እስከ ፍፃሜ ሕይወቷ ድረስ! ይህን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያለው የኢትዮጵያ ሴት ሕይወት በቅርብ ለተመለከተ ሌላ ታዛቢ፥ በእርግጥ ኢትዮጵያ ሀገራችን እራሷን ለመለወጥ ምን ያህል እርምጃ ማድረግ እንዳለበት ለመገንዘብ አያዳግተውም:: ከላይ ለአብነት የተጠቀሰው በኢትዮጵያ የገጠር ነዋሪቷን ሕይወት ማሳየቱን ከመደምደማችን በፊት፤ በአንድ ሀብታም ቤት በምታገለግል አግልጋይ ሴት ላይ የሚፈፀመውን ግፍም ማስታወስ ያስፈልጋል:: በየብሔረሰቡ ደግሞ የሴቶች ኑሮ በያይነቱ በመከራ የታጀበ ለመሆኑ ያለውን ልምድና ሁኔታ ማጤኑ ብቻ ይበቃል::

የገጠሯን ኢትዮጵያዊት መራራ ህይወት ስንዘክር፥ በከተማ የምትኖረዋ ሴት ህይወት የተሻለ ነው ማለት አይደለም:: የዚችኛው ኑሮ ደግሞ ለውርደትና ለዘመናዊ ባርነት የተጋለጠ ነው:: በከተማ የሥራ ማጣቱን ተንተርሶ ከሚመጣ የኑሮ ውድነት ጋር በተየያዘ ክስተት፥ በከተማ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያት የልብ ጠባሳን ብቻ ሳይሆን የአዕምሮ ሰቆቃንም ጭምር በሚያስከትል ቁጭት ተዘርዝሮ የማያልቅ ግፍና በደል ይፈፀምባቸዋል:: የሚቀምሱት የሚልሱት በማጣታቸው ምክንያት ሳይወዱና ሳይፈቅዱ፥ ኢትዮጵያዊ ባህላቸውን ብቻ ሳይሆን ክብር ሰብዕናቸውን ጭምር በሚያዋርድ ተግባር መሰማራታቸው ዓለም ያወቀው አንዱ መለያችን ሆኗል:: ዛሬ በከተማ የሚታየውን የሀገራችንን ሴቶች ሁኔታ በቅርብ ለሚከታተል ማነኛውም ሰብዓዊ ፍጡር፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደተዋረደችና ማንነቷም እየጠፋ መሄዱን በቀላሉ ይገነዘባል:: ይህ ትውልድ ትኩረቱ፥ በሀገር የማዳን ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በማንነት ፍለጋ ላይም ጭምር እንደሆነ መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም:: ዛሬ አንድ ኩሩ ኢትዮጵያዊ አባት፥ ለአቅም ሄዋን ያልደረሰችውን ሴት ልጁን፥ " እባክሽ ልጄ ወንድሞችሽና እህቶችሽ በረሃብ ከሚያልቁ እስቲ ወጣ ብለሽ

አንድ ነገር ፈልጊ" ማለት ያልተለመደ እንዳልሆነ ልባቸው የደም እምባ እያደማ የሚፀፀቱ አዛውንቶች ቁጥር በቀላሉ የሚገመትአይደለም። ይህ በሴቶች ላይ የሚከናወነው ጉድና ብሔራዊ ውርደት ከሀገር ውስጥ አልፎ ተርፎ የዓለም አቀፍ መልክና ድርጊት እያያዘ ከመጣ ዓመታት አስቆጥሯል። ዛሬ ሀገራችን የመንግሥት ሥልጣን ጨብጫለሁ በሚለው ወራዳ ዘረኛ ቡድን ተባባሪነትና ግፊት፥ በአያሌ ሽህ የሚቆጠሩ ወጣት ሴቶች ለዘመናዊ ባርነትና ሴትኛ አዳሪነት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች እንደ ንግድ ሸቀጥ የይለፍ ሰነድ እየተሰጣቸው በመጉረፍ ላይ ናቸው፡ በሌባኖስ ዋና ከተማ በቤይሩት ብቻ ከሃያ አምስት ሽህ በላይ የሚሆኑ ወጣት ኢትዮጵያት ዜጎች እንደሚገኙ በሰነድ የተረጋገጠ ሃቅ ነው። በዐረብ ባሕረ ሰላጤ ሀገሮችና በዐረቢያ ሳውዲት የተሰደዱት በበርካታ ሽህ የሚቆጠሩት ኢትዮጵያውት ዜጎች የሚደርስባቸው በደልና ግፍ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አልሆነም። በቤይሩትና ባህሬይን ከተሞች በቤት አገልጋይነት የተሰማሩት ወጣት ኢትዮጵያውያት በአሠሪዎቻቸው የሚደርሰውባቸውን ኢሰብዓዊ ግፍ መሸከም እያቃታቸው ከስቃዩ ለመገላገል ሲሉ ከፎቅ ላይ እየተፈጠፈጡ ራሳቸውን የሚያጠፉት ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ከአንድ ዓመት በፊት በሳውዲት አረቢያ ከተማ በጅዳ ያለ ተገቢው ህጋዊ ፍርድ በስቅላት የተገደለችው ወጣት ኢትዮጵያዊት የሚዘገንን አፈፃፀም የዓለምን ሕዝብ ህሌና እንደረበሸው የቅርብ ትዝታ ነበር። በጣም የሚያሳዝነውና የሚያስተዛዘበው ደግሞ ይህን አሳዛኝ ግድያ መላው ዓለም ሲያወግዘው፥ የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሰዎች የዲፕሎማቲክ ተቃውሞ እንኳን አለማሰማታቸው ነው።

በኢትዮጵያ የረዥም ዘመናት የመንግሥታት ታሪክ፤ ዜጎቹን ለውጭ ባዕዳን ለዘመናዊ ባርነት እያሰለፈ ሲሰጥ የወያኔ አገዛዝ የመጀመሪያው ክብረ-ወሰን በመያዙ፥ እነመለስ ዜናዊ እንኳን ደስ ያላቸሁ የሚሏቸው የኢትዮጵያ ጠላቶች አሏቸው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በሁለንተናዊ ገጽታዋ፥ እየተዋረደች፥ እየተጠቃችና እየተጎዳች አለች። የኢትዮጵያ ሴቶች ጭቆና ከሀገራቸው ውስጥ አልፎ ተርፎ የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግሮ፥ በመካከለኛው ምሥራቅ በመዝለቅ የሴቶች ዜጎቻችንን መከራና ስቃይ በከፋ መልኩ እንዲቀጥል መደረጉ እየታየ እየተሰማ አንዳችም ርምጃ አልተወሰደም። ይህም በመሆኑ እነኝህ ዜጎች፥ በሴትነታቸውና ስብዓዊ ፍጡር በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸውም ጭምር እያፈሩና እያዘኑ መሆናቸው አካባቢውን የጎበኙ ሰዎች በትካዜ ይገልጹታል። ይህ ክስተት፥ ለሀገር ክብር፥ ለወገን መብትና ነፃነት፥ ለታሪክና ለባህል መቆርቆር ቀናዒ የሆነ መንግሥት እስከሚመጣ ድረስ በከፋ መልኩ አይቀጥልም ብሎ መመኘት እራስን ማታለል ይሆናል። የገጠርና የከተማ ነዋሪቷን ኢትዮጵያዊት ማክተሚያ የሌለውን፥ የመከራና የስቃይ፥ የውርደትና የሀዘን፥ ብሎም የጨለማ ህይወት ለአንዴና ለመጨረሻው ለማስወገድ ያለው ምርጫ አንድ ብቻ ነው። ይኸውም፥ የሴቶችን መከራ አራማጅ አገዛዝ አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማስፈን ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ከአለፉት ሠላሳ አምስት ዓመታት ጀምሮ፥ በከፍተኛ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ነውጥና ቀውስ ውስጥ ትገኛለች። ለዘመናት ስር የሰደዱ ብሔራዊ ችግሮቿም መፍትኄ ማግኘታቸው ቀርቶ፥ለመቅረፍ እንኳን አልተቻለም። ስር የሰደዱት ችግሮቻችን በላይ በላያቸው አዳዲስና ተጨማሪ ችግሮች ተደራረቡባቸው እንጅ የመፍትኄ ጭላንጭሎች ሊታዩ አልቻሉም። የችግሮቻችን ስፋትና ጥልቀት፥ ውስብስብነትና ክብደት የቱን ያህል አስቸጋሪ ከመሆናቸው የተነሳ፥ ከአንድ ሩብ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ትግል ቢካሄድም ፍንክች ሊሉ አልቻሉም። ምናልባት የሀገራችንን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች በየፈርጃቸው መገምገምና መተንትን ከተቻለ፥ የኢትዮጵያ የተለያዩ ኅብተረተስብ ክፍሎች፥ ብሔረሰቦችና የሴቶች ችግሮችም እንደዚሁ ሊስተናገዱ የሚችሉት፥ ከጠቅላላው የሀገሪቱ ሁለንተናዊ ችግሮች አፈታትና መፍትኄ አፈላለግ አኳያ መሆኑ ሁሉም የሚስማማበት ሐቅ ይሆናል። እንደ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰብና በርካታ ቋንቋዎች፥ ባህሎችና ዕምነቶችን በማስተናገድ የቆየች ሀገር፥የወደፊቱ ዕድሏና ርምጃዋ ዋስትና ሊኖረው የሚችለው፥ በእኩልነት የሁሉንም ዜጎቿ ፈቃድና ይሁንታ ያካተተ ሕብረተ-ሱታፌ ሲኖረው ብቻ ነው ብሎ በሙሉ ልብነት መናገር ይቻላል። ይህ ብሔራዊ ራዕይና

ሀገራዊ ተስፋ ወደተግባር ሊለወጥ የሚችለው ደግሞ በአንድ ቀን ዠምበር ብቅ ብሎ በሚሄድ፥ ቅፅበታዊ ሁኔታ ወይም ደግሞ በግርግር ሥልጣን በጨበጠ ቡድን ሳይሆን፥ በሕዝብ ማለትም ብዙኀኑ ሴቶች በተሳተፉበት ትግልና በተገኘ ድል በተመሠረተ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ሂደት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ የሚካሄድ የለውጥ ርምጃ ስር እየሰደደና የለውጡንም ዋስትና እያረጋገጠ ከተራመደ፥ ሀገሪቱ የለውጡን አዝመራ የምታይበት ዕድሏ የፋፋና የጎላ ይሆናል፡፡ ዜጎቿም ከውስጥ ጭቆናም ሆነ ከውጭ ውርደት ነፃ የሚሆኑበት ዕድላቸው ዋስትና ይኖረዋል፡፡ በሰው ልጆች ታሪክ ስደት ያልተለመደ አይደለም፡፡ ዜጎች ተወልደው በአደጉበትና በኖሩበት ሀገራቸው ሲከፋቸው ሲበደሉና የከፋ ሥርዓት ሲጨቁናቸው፥ የሥርዓቱ ሰለባ ላለመሆን በብዛት ለማምለጥና የተሻለም ህይወት ለመፈለግ ይሰደዳሉ፡፡ ለዚህም በዘመናት እንደ ታሪክ ማስረጃ እየተነገረ የኖረው ዘፀዓት ነው፡፡ የተስፋውን ሐገር በመመኘት ከምድረ ግብፅ መሰደድ! ይህንን የታሪክ ማስረጃ እንደማጠየቂያ መጥቀስ ካስፈለገ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብም የዐረመኔውንና የዘረኞችን ግፍና በደል ለመሸሽ ሀገሩን እየለቀቀ በመላው ዓለም መሰደዱ የታወቀ ነው፡፡ የኢትዮጵያወጣት ሴቶች በተወለዱባት ሀገራቸው የሚፈፀምባቸውን ግፍና በደል ለመሸሽ የሚያደርጉት የነፍስ አድን ጥረት ምክንያት ግን ከዚህ ጋር የሚነፃፀር አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ወጣት ሴቶች ያለፈቃዳቸውና ያለምኞታቸው ለዘመናዊ ባርነት እየተዳረጉ ናቸው፡፡ የዚህም ብሔራዊ ወንጀልና ሀገራዊ ውርደት ተባበሪ በመሆን ግንባር ቀደሙን ሚና የሚጫወተው የወያኔ ሥርዓት መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ ሴቶቹ ሀገራቸውን ለቅቀው የሚሄዱት ሀገር የተስፋ ሀገር ሳይሆን፥ የሲዖልና የገሀነመ-እሳት ምድር በመሆኑ ነው፡፡ ከአለፉት አርባ ዓመታት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ ምክንያቶች ሀገራቸውን በመልቀቅ በዓለም ዙሪያ በስደት ይኖራሉ፡፡ እንደ የሁኔታቸው፥ ጥረትና ትጋታቸው ሠርተው የመኖር ዕድል ሊኖራቸው ይችል ይሆናል፡፡ በዐረብ ሀገሮች ለባርነትና ለውርደት እንደተዳረጉት ወጣት ኢትዮጵያውያት ዓይነት የከፋና የተዋረደ ህይወት ይኖራሉ ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ታዲያ የዘንድሮውን የዓለም አቀፍ ሴቶችን ቀን ስንዘክር፥ በዓይን ህሌናችን የምናስታውሰው የሀገራችንን ሴቶች በደልና በተለይም በገጠር ኢትዮጵያና በመካከለኛው ምሥራቅ እጅግ በጣም ዘግናኝና አሳፋሪ ህይወት በሚኖሩና ከዚህም ስቃያቸው ለመውጣት ኤሎሄ! ኤሎሄ! በሚሉት ወገኖቻችን አሳዛኝ ጥሪና ለቅሶ ነው፡፡

የሀገራችን ሴቶች በትግሉ ሙሉ ተሳትፎን ካደረጉ የድል ቀን ለመቅረቧ ክርክር የሚያሻው አይደለም፡፡ በታሪክ፥ በክፉውም በደጉም ዮዲት ፤ጣይቱ ብጡል ብንልም ሴቶች በሥልጣን ቁንጮ በአዛዥነት ከፃፉት ታሪክ ባሻገር፥ የነበረውና ያለው ሲመረመር፥ ሴቶች በብዛት በሀገራዊ ትግሉ ለመሳተፋቸው ታሪክ ምስክር ነው፡፡ በአድዋ ጦርነት ለምሳሌ ከ 30 ሺ ያላነሱ ሴቶች በግንባር በልዩ ልዩ ዘርፍ ተሳትፈዋል፡፡ በሙሶሊኒ ወረራም ጊዜ ብዙ ሺ ሴቶች መሥዋዕትነትን ከፍለዋል፤ የአርበኝነት ግዳጅንም ተወጥተዋል፡፡ የአፄውን ሥርዓት ለመጣል በተደረገውም ረጅም ትግል ሴቶች ተመልካች ሳይሆኑ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ወጣት ሴቶች በወቅቱ ትግል በተደራጀ መልክ ተሰባሰብው ለመብታቸውና ለሀገራቸው ያደረገት ተጋድሎም የሚታወቅ ነው፡፡ በዚህ መስክ ኢሕአፓ፥ ሴቶች በራሳቸው ተደራጅተው ለመብታቸው እንዲታገሉ ከመጀመሪያው ጀምሮ የቆመ ሲሆን፥ ሴቶች በነፃ የመደራጀት መብታቸው መከበሩም ከድላቸው ጋር የተቆራኘ መሆኑንም ጫና ሰጥቶ ተሟግቷል፡፡ በመሠረቱ የሴቶች መብት መከበርና እኩልነት መረጋገጥ ከአጠቃላይ ኅብረተሰቡ ነፃነት ጋር የተየያዘ ቢሆንም፥ ሴቶች የራሳቸውን መብት ለማስከበር በራሳቸው ተደራጅተው ነፃ አውጪ ነን ከሚሉና ገና ለትምክህት ተገዢ ሊሆኑ ከሚችሉትም ራሳቸውንም ለመጠበቅ ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ ፋሺስቱ ደርግ የሴቶችን በራሳቸው የመደራጀት መብት ሰርዞ በራሱ ቁጥጥር ስር የሴቶች ማበር/ አኢሴማ/ ለማቋቋሙ ሌላ ታጋይ ሴቶችን መጨፍጨፉ ታሪክ የመዘገበው አሰቃቂ ሀቅ ነው፡፡ደርጉን የተካው ጠባብ ድርጅትም ለሴቶች መብት አፋዊ ድጋፍን እየሰጠ በተጨባጭ ግን የሴቶችን በነፃ የመደራጀት መብት አፍኖ ሴቶችን በሸቀጥ ደረጃ እየሸጠና እያዋረደ ያለ መሆኑን ደግመን ደጋግመን የገለፅነው ነው፡፡ በአሁኑ አገዛዝ፥ ሴቶች ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ለጭቆናና ብዝብዛ አልፎም ለቀሳፊ በሽታና ለውርደት የተጋለጡበት ነው፡፡

በሕግ ደረጃና በወረቀትም ሰፍረው የሚለፈፍላቸው መብቶች በገቢር ላም አለኝ በሰማይ መሆናቸው በተለይም ሴቶችን በተመለከተ የተረጋጋጠ ነው:: የአገዛዙ ቁንጮዎች የሴቶችን መብት በመድፈርና በመርገጥ ዋነኞቹ ናቸው:: ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሴቶች ሳይቀሩ እየተደፈሩና ለጋብቻም እየተሰጡ ናቸው:: ሴትኛ አዳሪነትም የእነሱም ዕጣ ሆኗል:: ለመንገድ አዳሪነት ከተጋለጡት ብዙ ሺዎች ሴቶች-ያውም ህፃናት ሴቶች ብዙዎቹ ናቸው:: በጋምቤላ፣ በአዲስ አበባ፣ በጎንደር፣ በአጋዴን፣ ወዘተ... የጠባብ ብሔረተኛው አገዛዝ አፈና ሰለባዎች ሴቶችም ናቸው:: ብዙ ሺ አበራሽ በርታዎች በዝዋይ፣ብር ሸለቆ፣ ዴዴሳና በየምስጢሩ ጉድጓዶች አሉ:: ሴቶች በሀገራችንና በሕዝብ ላይ የመጣውን መከራ ዋነኛ ተቀባዮች ናቸው:: የሴቶች ነፃነት ገና ገና ነው:: ከግማሽ ባለይ ሕዝብ ፍዳ እየተቀበለ ደግሞ በሀገሪቷ ዴሞክራሲ ሰፍኗል ማለት ዘበት ነው:: በመሆኑም የሀገር ትግል ድልን ይመታ ዘንድ የኢትዮጵያ ሴቶች በትግሉ መሳተፋቸው ወሳኝ ነው:: በደፈናው በትግሉ ይሳተፉ ማለት ሳይሆንም በሚገባ መብታቸው ታውቆና ተከብሮ የትግሉ አካል መሆን አለባቸው ማለት ነው:: ተወደደም ተጠላም የፖለቲካው መድረክ የወንዶች ብቻ መስሎ ከመታየቱ ሌላ ያ ሁሉ ትግል ተካሂዶ ዛሬ ግን የኋልዮሹ እንቅስቅቅ የገነነበት ሁኔታ በመኖሩ ሴቶችን በተመለከተ አደኃሪና ኋላ ቀር አቅዋሞች ያንሰራሩበት ሁኔታ አለ :: ለሴቶች መብት መከበርድምፅ ያላሰሙ ሴቶች ወሊድን መቆጣጠር መብት አይገባቸውምብለው ሲለሰለፉ ለመታዘብ በቅተናል:: የሀገር ህልውና በወያኔ ሲካድ ፀጥ ያሉ ሴቶችን እየጎዱ ያሉ ኋላቀር ባህሎች ይወገዱ ሲባል ግን የባህል ጠበቃ ሆነው ሲጯጯሁ ለማድመጥም ተገደናል:: የግማሽ ሕዝብን መሠረታዊና ሰብዓዊ መብት የሚፃረሩ ልምዶችና ባህሎች መወገድ ወሳኝ ሆኖ ሳለ ባህላችን በሚል ፈሊጥ የህፃናትን መብት ሳይቀር የሚቃወሙ እንዳሉም አይተናል:: በዚህም የተነሳ የሴቶች መብት በመረገጡ ኅብረተሰቡ ራሱ ኋልዮሽ እየተጎተተና የነፃነትና የመብት ትግሉም እየተሽመድመደ ይገኛል::

ይነስ ይብዛ ሴቶች ወደ ትግሉ ጎራ እየተሳቡ መሆናቸው ይታያል:: በሀገር ወዳድ ድርጅቶች ተሳትፏቸው ጨምሯል:: በ 1997 ግንቦትና ሰኔ የከፈሉት መስዋዕትነት ብቻ የቅርብ ምስክር ነው:: በራሳቸው በዓለም አቀፍ ደረጃም ለመደራጀት ጀምረዋል:: የወያኔን የብሔረሰብና የሃይማኖት አጥር በመጣስ ሴቶች በፆታቸው ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸውም መሰባሰብ መጀመራቸው ለወያኔ አደገኛ ነውና ሐቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችን ሊያፈርስ እንደጣረው ሁሉ የእነሱንም ጥረት ሊያደናቅፍ መሞከሩ የሚጠበቅ ነው:: የአስተማሪዎች ማኅበር፣ የሠራተኞች ማኅበር፣ የተማሪዎች ማኅበር ወዘተ... ላይ የደረሰው አፍራሽ ምት በቂ ምሳሌ ነው:: ነፃ ማኅበራትና ወያኔ ሆድና ጀርባ ናቸው:: ለዚህም ነው ሴቶች በአመቺው መንገድ ሁሉ በፆታቸው መደራጀታቸው ለትግላቸውና ለሀገራዊ ትግሉ ወሳኝ እርምጃ ሆኖ የሚገኘው:: ይህ ድርጅትም የምርጥ ሴቶች ስብስብ ሳይሆን፥ የገጠሯን እህትና እናት ያካተተ ሰፊ ደርጅት መሆን የሚገባው ከመሆኑ ሌላ የትግሉንም መሠረትና ይዘት በሚገባ ያጤነ፣ የሴቶችን የመብት ትግል ከሀገር የነፃነት ትግል ጋር በሚዛን ያቆራኘ፣ የሴቶች ድርጅትን ነፃነት ያስከበረ መሆን ይኖርበታል:: ወንዱ ዜጋ፥ በተለይም ፖለቲካ ድርጅቶች በበኩላቸው ደግሞ አለሴቶች ተሳትፎ ሀገራዊ ትግሉ ድልን አንደማይቀዳጅ በማመን የሴቶችን ጥረትና ትግል በቀና ልቦና በመደገፍ ለማጎልበት መጣር ግዴታቸው መሆኑን መቀበልና በሥራ ማዋል አለባቸው:: ትግላችን የጋራ ነው፣ አገዛዙ ፆታ ሳይለይ ሁሉንም የሚጨቁን ቢሆንም፥ ሴቶች ደግሞ በፆታቸው የተነሳ የሚደርሰባቸው ልዩና ሁሉን የሚመለከት ጭቆና መኖሩ በሰበሰብ አሰባቡ ሊሸፈን- ሊካድ የሚገባው አይደለም::

ኢትዮጵያን ከወያኔ ጭቆና ነፃ ማውጣት ከፈለግን የኢትዮጵያ ሴቶች ተደራጅተው የትግሉ አካል መሆን አለባቸው:: ችሎታቸውንና ሚናቸውን የሚክዱ ባህሎች፣ ልምዶች፣ ተረቶችና አቋሞች ሁሉ መወገድ አለባቸው:: የሴቶችን እኩልነት መካድ፥ ለወንዱ ይዞታ መዛባትና መዘባረቅ ምክንያት ነው:: የሴቶች መብት

**መከበር ለወንዱም ነፃነት አስፈላጊ ነው። ለዚህም ነው፥ ኢሕአፓ ዛሬም እንደ ትላንቱ ከሩቁ የሚያስተጋበውን የድርብ ጭቆና ታጋዮች እሮሮ አዳምጠን ሊደራጁና ሊታገሉ ሲነሱ ከጎናቸው ቆሚያለሁ እንቁም የሚለው።**

**በሀገራችን ፍትህ፣ እኩልነትና አንድነት ዕውን እንዲሆኑና እናቶችና እህቶች ከድርብ ጭቆና ይላቀቁ ዘንድ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በጋራ እንታገል!!!**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፋፋዩና ከዘረኛው አገዛዝ ለማላቀቅ ትግላችንን እንፋፍማለን!!!!**